# <u>ከአኘዋክ የሀዘን ድንኳን ወደ ኢትዮጵያ ልቅሶ ዳስ፡ የአባንግ ጉዞ</u>

## የታክሲ ነጂው መገረም፡ ኢትዮጵያዊ የማይመስል ኢትዮጵያዊ

አበዛኸው እንዳትሉኝ። ይሄ: መነገር ያለበት ታሪክ፤ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ልናውቀው የሚገባ ክስተት ስለሆነና አላደርስ ስላለኝ ነው ተመልሼ የመጣሁት። የዛሬ አራት አመት አካባቢ፡ አንድ ጥቁር ያለ (“ቁ” ይጠብቃል)፡ “ኢትዮጵያዊ የማይመስል” ኢትዮጵያዊ፤ ሌላ ኢትዮጵያዊ የሚመስል ኢትዮጵያዊ በሚያሽከረክረው ታክሲ፡  ከአንዱ የዋሽንግተን ዲ.ሲ. አውሮፕላን ማረፊያ ወደ መሀል ከተማ ይጓዛል። መሰለኝ። በእንግሊዘኛ ንግግር ጀመሩ። “ከየት ነህ?” ታክሲ ነጂው ጠየቀ። “እስኪ ገምት ከየት እንደሆንኩ።” መለሰ ተሳፋሪው። “ከሱዳን?”። “አይደለሁም።” “ከኬንያ?” “ተሳስተሀል። ሞክር።” “ከጅቡቲ፤ ከኤርትራ፤ ከዩጋንዳ።” ሁሉም የምስራቅ አፍሪካ አገሮች ተጠርተው አለቁ። ኢትዮጵያ አልተጠራችም። ኢትዮጵያ ከቶም አልታሰበችምም። ያ “ኢትዮጵያዊ የማይመስለው” ኢትዮጵያዊ ግን ከኢትዮጵያ ነበር። የታክሲው ሹፌር፡ ያ ያሳፈረው (የጫነው) ጥቁር ሰው፡ እንኳዋንስ መጀመሪያውኑ ከኢትዮጵያ መሆኑን ሊገምት፡ ቀድሞውንም ነገር፡ ከኢትዮጵያ ነኝ ካለው በኋላ፡ ሊያምን አልቻለም። እንዲህ አለ አባንግ “ጨርሶውንም ኢትዮጵያዊ እንደማልመስል፡ የዋሁ ኢትዮጵያዊ በየዋህነት ኢትዮጵያዊ ልሆን እንደማልችልም ነገረኝ።” አባንግ ፖለቲካዊ ንዝረት ተሰማው። አልተቀየመም። ግን ደግሞ ይህ ነገር አልተዋጠለትም። ችግራችን ከመንድርም ባሻገር የአገር እንደሆነ ተረዳ። ስለዚህም ያ የአኘዋክን ብቻ ጉዳይ ሙጭጭ አድርጎ ይዞ የነበረው አባንግ፡ የጉዞውን አድማስ ከአኘዋክ ሰማይም በላይ ካላሰፋውና ሌሎች እንደዚያ ታክሲ ነጂ ያሉትን ኢትዮጵያዊያን ሁሉ መድረስ ካልቻለ፤ ባንድ ቤት ውስጥ እንደሚኖሩ ግን እንደማይተዋወቁ ያንድ እናት ያንድ አባት ልጆች ልንሆን ነው፡ ብሎ አጀንዳውን አሰፋው። እነሆ ያኔ መገስገስ የጀመረው የአባንግ የትግል ባቡር፡ ዛሬ ከሜኒሶታ እስከ ለንደን፡ ከዲሲ እስከሲያትል፡ ከአኘዋክ እስከ ባህርዳር፡ ከአምቦ እስከ ሀረር፡ ከኦጋዴን እስከ ጋምቤላ፡ ከቶሮንቶ እስከ ሳስኬችዋን እየገሰገሰ ነው። የሚያጅበው ካለ ይከተለው። የማይከተለውም ይከተለው። ሰሞኑንም አባንግ ሲበር ነበር። ማስረጃ ሲያጠናቅር፡ ማስረጃም ሲያቀብል፡ ለኢትዮጵያ ከቆሙና ገንዘብ ከማይጠይቁ ጠበቆች ሲመክር፡ ሲሰለፍ ሲያሰልፍም ነበር። ስለአባንግ ዓላማ ወርቃማነት፡ እኔ ብቻ አይደለሁም፡ አልም መስክሯል፤ አለማየሁ፡ ፕሮፌሰር።

**ፕሮፌሰር አለማየሁን ሰጠን**

“ከፋት በላያችን እንዲሰለጥን የሚያስችለው፡ የኛ የሴቶቹና የወንዶቹ እጅ አጣጥፎ መቀመጥ ነው” ይላል የፕሮፌሰር አለማየሁ የዘወትር ኢሜል ማሳረጊያ። ባለፈው ሰሞን በጻፈው፡ “ጎበዝ እንግዲህስ መለያየት ይቅር፡ ልባችንንና አእምሮአችንን ከፍተን ተጨባብጠን ወደ ስራ እንግባ” በሚለው ጽሁፉ የጋራ ንቅናቄ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የያዛቸውን መርሆችና ዋና ዋና እምነቶች ደግፎ መጻፉ እጅግ አስደስቶናል ይላላ የጋራ ንቅናቄው ያወጣውና አቶ አባንግ አሳምሮ ያቀረበው ጽሁፍ። የሲያትሉ ወዳጃችን አቶ ሼክስፒር ፈይሳ ባለፈው ዓመት ሲያትል ንግግር ሊያደርግ የመጣውን ፕሮፌሰር አለማየሁ ገብረማሪያምን ሲያስተዋውቀው እንዲህ ብሎ ነበር። “ብዙ ሰዎች ፕሮፌሰር አለማየሁ ገብረማሪያም ምንና ማን እንደሆነ ብዙ ነገር ሲናገሩ ይደመጣል። እኔ ግን ምን እንዳልሆነ ነው የምነግራችሁ።” ሼክስፒር ቀጠለ፤ “ፕሮፌሰር አለማየሁ በቀን ውስጥ ከሀያ አራት ሰአት በላይ አለው ይላሉ። ነገር ግን ያ ሀሰት ነው። ልክ እንደኛ እሱም በቀን ውስጥ ሀያ አራት ሰአት ብቻ ነው ያለው። በነዚያ ሰኣታት ውስጥ ነው የሚሰራውን ሁሉ የሚሰራው።” ይሄ ፕሮፌሰር አለማየሁ ገብረማሪያም እንደጉድ ይጽፋል። አይሰለቸውም። እኛ ብንጣላ፡ ብንባላ፡ ብንቃላ፡ ተስፋ አይቆርጥብንም። እነሆ ባለፈው ሰሞን በጻፈው አብይ ትንታኔም እንግዲህስ የርስ በርስ ንትርካችንን ትተን ወደስራ እንግባ አለ። በዚያ አላቆመም። ይሄ በዚህ በመከራችንና ብዙ አዋቂዎች ኮርተው ወይም አኩርፈው ጥግ ይዘው በተቀመጡበት ሰአት ከጎናችን የቆመ ታላቅ ፕሮፌሰር፡ እነዚያ የጋራ ንቅናቄ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የንቅናቄያችን ምሰሶዎች ብሎ የሚላቸውን ሁለት አብይ መርሆች ማጽደቁ አባንግን ጨምሮ መላውን “የጋራ ንቅናቄ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ” በደስታ እንዲዘል አድርጎታል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲ ለማምጣት የምናደርገው ትግል፡ ልዩነቶቻችንን አሁን የምናጎላበት ሳይሆን ለሌላ ዘመን ለሌላ ግዜ የምናስቀምጥበትና በግልጽ ለእውነተኛ ለውጥ የምንተጋበት አዲስ አቀራረብና ስልት ይሻል። ፕሮፌሰር ቀጠለም፤ ትግላችንን የሚቃኙት ዋናዎቹ ርእዮታችን በሁለት መሰረታዊ ፍልስፍናዎች ላይ መሰረት መጣል አለባቸውም አለ። ይሄንን እንዳሻችሁ ትተርጉሙት ዘንድ በእንግሊዘኛው እንዳለ ብናስቀምጠው ይሻላል። <u>***1) OUR HUMANITY MUST ALWAYS RISE ABOVE OUR ETHNICITY, NATIONALITY, RELIGIOSITY, AFRICANITY OR ETHIOPIANITY. 2) NO ONE CAN BE TRULY FREE IN ETHIOPIA UNLESS ALL ETHIOPIANS ARE FREE***. *IF WE SUBSCRIBE TO THESE TWO CORE PRINCIPLES, OPEN OUR MINDS AND HEARTS AND COLLECTIVELY PULL TOGETHER, WE WILL SOON FIND OURSELVES IN A WIN-WIN SITUATION.*</u>

አንደኛ ነገር፡ ሰብአዊነታችን፡ ወይንም ሰው መሆናችን ከጎሳችን፡ ከብሄራችን፡ ከዘራችን ከሀይማኖታችን ከአፍሪካዊነታችን፡ ይቅደም። ሁለተኛ ነገር፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ሁላችንም አብረን ነጻ ካልወጣን፡ ማንም እውነተኛ አርነት አይወጣም። ኢትዮጵያ ነጻ አልወጣችምና የትግራይ ነጻነት ግንባር አርነት ብሎ ይነሳ እንጂ፡ ያ የተነሳበትን አርነት ገና ህዝቡ አልደረሰበትም ነው። ነገም የእገሌ ነጻ አውጪ፡ የእንቶኔ ነጻነት ግንባር ብለን ብንነሳ፡ ኢትዮጵያ ነጻ እስካልወጣች ድረስ፡ እውነተኛ የእገሌ ነሰ የእንቶኔ ነጻነት አይኖርም። ሁላችንም ባርነት ውስጥ ነን አይነት ነገር። ለነዚህ ሁለት መሰረታዊ መርሆች የተገዛን እለት ነው ሁላችንም አሸናፊ የምንሆነውና ተሸናፊ የማይኖረው። የናፈቀንም አሸናፊና ተሸናፊ የሌለበት፡ የምናሸንፈው ዋናውን ጠላት ድንቁርናና አምባገነንነትን ብቻ የሆነበት አገር/አለም ማግኘት ነው። ያንን ደግሞ አባንግ እንደመጥምቁ ዮሃንስ በዚህ በኛ የመለያየት በረሀ ይሰብካል።

**የጋራ ቀንበር: የጋራ መከራ፤ ስለቃላችንና ተግባራችን መገጣጠም አስፈላጊነት**

አንዱ ላንዱ የሚቆምበትና በጋራ የምናሸንፈበት መድረክ ስላስፈለገ ነው ይሄ የጋራ ንቅናቄ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የተጸነሰው፡ የተወለደውም። የአኝዋክ የሀዘን ድንኳን በተጣለ ግዜ፡ አባንግ አኝዋኩ ከጥቂቶች ጋር ተሰለፈ። የኦሮሞ ተወላጆችም በተገደሉ ግዜ ኦሮሞው ለብቻው ተሰለፈ። ሌላውም እንደዚያው ቀጠለ። ስለዚህም፡ ያ የዋህ ታክሲ ነጂው በየዋህነት ኢትዮጵያዊ እንደማይመስልና ሊሆንም እንደማይችል የነገረው አባንግ፡ ችግራችን ስር የሰደደ፡ ከላይ ከምናስተውለውም በላይ የጠለቀ እንደሆነ ተሰማው። ስለዚህም ኢትዮጵያዊያንን ሁሉ መድረስ ካልቻለ፡ እሱ ብቻውን የሚጓዘው ጉዞ፡ እሱንም ይሁን አኝዋክን እንዲሁም ታክሲ ነጂውን ኢትዮጵያዊ ከአውደ ነጻነት እንደማያደርሳቸው ተረዳ። ሁላችንም በጋራ የምንሰበሰብበት መድረክ እንደሚያስፈልግ አመነ። መልኩ እኛን የማይመስል፡ ቋንቋውም ከኛ የተለየም ኢትዮጵያዊ፡ ኢትዮጵያዊ መሆን የሚችልበት የጋራ መድረክ እንደሚያስፈልግ አመነ። የሚያምኑትም ሁሉ ተሰባሰቡ። እነሆ የጋራ ንቅናቄ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ ተወለደ። ያ ንቅናቄ የተመሰረተባቸውን መርሆች ነው ፕሮፌሰር አለማየሁ በብእሩ ይሁን፡ ይደረግ፡ ይደልወ ይደልዎ፡ ያለው።

አልዋሻችሁም፡ ከአባንግ ጋር አልፎ አልፎ በስልክ እንጫወታለን። ስለኢትዮጵያ ያለውን ራእይ ሲነግረኝ፡ ስለኢትዮጵያ የሚያልመውን ሲተርክልኝ፡ ስለአገሩ የሚጸልየውን ጸሎት ሲደግምልኝ ስሰማው ብውል አልጠግብም። ተንኮል የለውም። ክፋትም የለውም። ስለድርጅቶች ክፉ አይናገርም። ይሄ እኛ ጋር የከረውና ያነፈረን፡ ቆዳችንን ያደነደነው የርስ በርስ ሽኩቻ እሱ ጋር የለም። አባንግ አባንግ ነው። እነሆ በዚህ በወርኀ ሰኔ፡ ከሀያ ቀን ጉዞው ተመልሶ መጣ። ዘገባወን ሰጠን። አባንግን ለማድነቅ የግድ ከሌሎች ፖለቲካ መሪዎች ጋር ማወዳደር የለብኝም። ግን ዘወትር የሚያስደንቀኝ ተፈጥሮ አለው። የኢትዮጵያ ፖለቲካ ድርጅቶች የስራ ሪፖረታቸውን በስነት መከራ በስንት ጉትጎታ ነው የሚያቀርቡት። ለዚያውም ካላቸው ነው። አባንግ ግን በየሳምንቱ ወይም እያሰለሰ የሚለውና የሚናገረው አያጣም። ዘወትር የአባንግን ኤሜል ስናነብ፡ ከመጨረሻ ላይ እንዲህ ይላል። “ብዛት የማሸነፍ ወይም ለማሸነፍ ወሳኝ አይደለም፤ ይልቅስ በህዝብ ህሊና ውስጥ ሰደድ እሳት ለመለኮስ የሚተጉ የማይደክማቸውና የተቆጡ ጥቂቶች እንጂ።" IT DOES NOT REQUIRE A MAJORITY TO PREVAIL, BUT RATHER AN IRATE, TIRELESS MINORITY KEEN TO SET BUSH FIRES IN PEOPLE'S MINDS" BY SAMUEL ADAMS። እነሆ ያለውን፡ የሚናገረውን የሚሆንና የሚያደርግ አባንግ ነው። ጥቂት ደጋፊዎች ይዞ ስራውን እየሰራ ነው።

**<u>አባንግን እናፍጋው፡ ምክንያቱም አባንግ ራሱን ሰጥቷላ፡</u>**

ከዚህ በፊት ስለአባንግ ተጽፎ ነበር። HTTP://WWW.ECADFORUM.COM/FILES/EDITORIAL_ABOUT_OBANG.PDF ። የአባንግ ዓላማና መርህ እዚያ ላይ ቁልጭ ተደርጎ ተቀምጧል። አባንግ “ሰብአዊ ብሄርተኝነትን” ያራምዳል። አባንግ ብዙ ፖለቲካዊ ሀረጎችን ተክሏል። “መንደር ወይስ አገር?” ይላል። “HUMANITY BEFORE ETHNICITY” የሚለው ነገርም አለው። ሽናሻነት፡ ከፊቾነት፡ ኦሮሞነት፡ አማራነት፡ ትግሬነት አኙዋክነት ከዚያ ለጥቆ የሚመጣ ነው። አባንግ ኢትዮጵያዊያን ሲል፡ ማንም በኢትዮጵያ ድንበር ውስጥ የሚኖርን ሰው ነው። ሰውነት፡ ይላል አባንግ “IS A GREAT UNIFIER THAT GOD GAVE TO US WHEN HE CREATED US—ALL OF HUMANKIND—IN HIS IMAGE, MAKING US ALL OF EQUAL VALUE, REGARDLESS OF THE SUPERFICIAL DIFFERENCES BETWEEN US.” አባንግ ዜና አንብቦ ብቻ ቤቱ የሚቀመጥ ሰው አይደለም። ሰው ተገደለ፡ ሰዎችም ተጨፈጨፉ ሲባል ሰምቶ ቤቶ ገብቶ አማን የሚያድር ሰው አይደለም። ዜናውን ተከትሎ እርምጃም ይወስዳል።

በቅርቡ በጻፈልኝ ምይል ላይ እንዲህ አለኝ፡ “I STRONGLY BELIEVE THAT THE KILLING, SUFFERING, CORRUPTION, HUMAN RIGHTS ABUSES AND THE KILLING IN ETHIOPIA MUST STOP.” “ተክሌ፡ በኢትዮጵያ ውስጥ የሰፈነው ግድያ፡ ስቃይ፡ ሰብአዊ መብት ገፈፋ፡ ሙስና መቆም አለበት።” ለዚህም ነው፡ በዚህ ባሳለፍናቸው ጥቂት ሳምንታት ውስጥ አባንግ፡ በወዳጆቹ ረዳትነት ከዋሽንግተን ኦታዋ፡ ከቶሮንቶ ዳላስ ተንቀሳቅሶ በአወሳ፡ በቴፒ፡ በአኝዋክ፡ በኦጋዴን፡ በአፋር በቤንሻንጉል፡ በአምቦ፡ በጅማ፡ በአዲስ አበባ፡ በቦረና በሌሎችም ቦታዎች የተፈጸሙ የዘር ማጥፋትን በሺሆች የሚቆጠሩ ማስረጃዎችን ሰብስቦ፡ ለጄኖሳይድ ዋች

ፕሬዚዳንትና ይሄንን ጉዳይ በነጻ ለያዙት አራት አለም አቀፍ ጠበቆች አስተላልፈዋል። ማስረጃ የማሰባሰቡ ስራም ይቀጥላል ብሏል። ኦባንግ የካናዳና የአሜሪካ መንግስታትንም መጎትጎቱን ቀጥሏል። ኦባንግ እዚህ *WWW.SOLIDARITYMOVEMENT.ORG* ይገኛል።




የኔ ሀሳብ እንግዲህ እንዲህ እንደሚከተለው ነው። ትግላችን ግቡን የማይመታበት አንዱ ምክንያት "የሙሉ ጊዜ ጠላትን በትርፍ ጊዜ ስለምንዋጋ ነው።" እንደ ኦባንግ ያለ ሰው ግን የኢትዮጵያን ጉዳይ የትርፍ ጊዜው ስራ አላደረገውም። የሙሉ ጊዜ ጉዳዩ ነው። ይሄ ግን አይቀጥልም። ኦባንግ የኛን እጅ ይፈልጋል። ይሄንን ኦባንግ አላለኝም። ግን ባይለኝም አውቀዋለሁ። ኦባንግ የረዱትንና ጉዞውን የሸፈኑለትን ሁሉ አመስግኗል። ኦባንግ ራሱን ከሰጠ፡ እኛ ደግሞ ከራሳችን መለስ፡ ያለንን ልንሰጥ ግድ ይሏል። ተራ ገብተን፡ በወረፋ ኦባንግን ማፍጋት አለብን። ኪሳችንን ይጭነቀው እንጂ። እንደኦባንግ ያለ ማንም የለም አልልም። ግን እንደኦባንግ ያለ ማንም አይታየኝም።

ልጅ ተክሌ ነኝ፡፡ ካናዳ፡ አስተያየት ለመስጠት ወይም ለጥያቄ በዚህ ECADF@ECADFORUM.COM
OR INFO@ECADFORUM.COM ያግኙን።